# እግሬ

ትውልድ  በትውልድ አድሞ ወገን በወገን ተነስቶ
ልጅ በወላጅ ጨክኖ
ወንድም እህቱን ኮንኖ
በስመ ርእዮተ ዓለም ሰው እርስ በርሱ ተበላልቶ

በልጅ አዕምሮየ ይህን  ታዘብኩና
የሕይወት ላይ ታቹ ተዛባብኝና
ሐቁና ውሸቱ ተቀላቅሎብኝ
ጭንቅላቴ ደክሞት አንቀላፍቶብኝ
መሪውን ለቅቄ ለእግሬ ሰጠሁኝ

እግሬም ብርቱ ነበር በረረ ከነፈ
ለአንዳፍታም ቢሆን ከቶም አላረፈ
ከበቀልኩት ላላድግ ዕድሌ ሆነና
'ሀ' ብዬ ጀመርኩኝ የስደት ጎደና

ያ መከረኛ እግሬ ጎትቶ ወስዶኝ
ትንሽ ላጫውታቹህ የት እንደጣለኝ

ትልቅ አያከብሩ ሽማግሌ አዛውንት
የጉድ ጉግ ማንጉጎች ነጫጭ ሰይጣውንት
ሃይማኖተ ንዋይ እምነታቸው ባዶ
እዚህ አደረሰኝ እግሬ ሄዶ ሄዶ

አያስቅ ቀልዳቸው ቋንቋቸው መከራ
ቅርስ ታሪክ የላቸው ለልጅ የሚወራ
የትውልድ ውርሻ የትውልድ አደራ
መጠሪያ የላቸው ከስማቸው ሌላ
እዚህ ጣለኝ እግሬ የኋላ የኋላ

ዘፈናቸው አይጥም አያውቁ ጨዋታ
የጩኸት ትርምስ ቅጥ የለሽ ጫጫታ
ወኔ አይቀሰቅስ አያስመታ እስክስታ
ቀረርቶም አይሉት አያስጨብጥ ቃታ
የወሮች ገበያ የዝንጀሮች ሆይታ
እዚህ ጣለኝ እግሬ የማታ የማታ

የገሞራ ልጆች የሶደም ዝርያ
የስይጣን ተገዡች የሳጥናኤል ባርያ
ግብረገብ አያውቁ ሞራል የሌላቸው
ቁሳቁሱን ሰጥቶ ፍቅር  የነሳቸው
ጓደኛ እማይሆኑ ከእምነት የራቁ
የቅንጣትም ያክል ላደራ ማይበቁ
ሊናቁ ሲገባ ሰውን የሚንቁ
የኔ ተሽካሚ እግሬ ባለአደራ
ውሎየን አረገው ከነዚሁ ጋራ

ካሳ በ. በላይ

ይቀጥላል...